# እ.ኤ.አ ከ ኦክቶበር 21-31/2018 የነበረው


# የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በአብዛኛዎቹ የሰሜን እና መካከለኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የወቅቱ ደረቅ፣ ፀሃያማና ነፋሻማው የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ነበር የተስተዋለው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍረዎች ላይ የለሊት እና የማለዳው ቅዝቃዜ ጨምሮ ተስተውሏል፡፡ በሌላ በኩል በምስራቅ፣ በደቡብ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች አልፎ አልፎ የተሻለ የደመና ሽፋን ነበራቸው፡፡ በዚሁ መሰረት ምዕራብ እና ደቡብ ኦሮሚያ፣ ጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ደቡብ ሱማሌ እና ምስራቅ ኢትዮጵያ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ አልፎ አልፎ ከነበራቸው የደመና ሽፋን ደቡብ አፋር፣ ምስራቅ አማራ እና መካከለኛው የሀገሪቱ አካባቢዎችም በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ ዝናብ ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ ቦታዎች ላይም ከባድ ዝናብ እንደተመዘገበ ያገኘናቸው የዝናብ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ለመጥቀስ ያህል በአቦቦ 33.2፣ በዶሎመና 46.5፣ በዲላ 31.4፣ በጊኒር 68.0፣ በማጀቴ 30.2፣ በቴፒ 35.2፣ በሞያሌ 41.6፣ በጊምቢ 39.6፣ በባሌ ሮቤ 42.3፣ በአሶሳ 59.4፣ በሲርበ አባያ 40.2፣ በአለም ተፈሪ 47.5፣ በገዋኔ 46.6፣ በማጂ 30.2 እና በዋንብራ 30.8፣ በሚ.ሜ ይገኑበታል፡፡


ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የነበረው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በሰሜን ጎንደር፤ አሶሳ እና መተከል፤ ከኦሮሚያ በቄለም ወለጋ፣ በምዕራብ ወለጋ፣ በኢሉባቦር እና ጅማ አርሲ እና ባሌ፣ ጉጂ እና ቦረና ዞኖች፤ በጋምቤላ፤ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሸካ፣ የከፋ፣ የቤንች ማጂ፣ የደቡብ ኦሞ፣ የሰገን ህዝቦች፤ ከሶማሌ የኖጎብ፣ የአፍዴር እና የሊበን ዞኖች ከ25-145 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ4-8 ቀናት ያህል የነበራቸው ሲሆን፤ በምዕራብ ትግራይ፣ በምስራቅ ወለጋ፣ በደቡብ ጎንደር እና በምዕራብ ጎጃም፣ በአፋር ክልል ዞን 03፣ በፋፈን እና ሲቲ ዞኖች ላይም ከ5-22 ሚ.ሜ ከ3 ላነሱ ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው (ካርታ 1 እና 2) ፡፡

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር በምዕራብ ትግራይ፣ በሰሜን ጎንደር፣ በቤንሻጉል-ጉሙዝ፣ በጋምቤላ፣ በቄለም እና ምዕራብ ወለጋ፣ በኢሉባቦር፣ በሸካ፣ በከፋ፣ በቤንች ማጂ፣ በደቡብ ኦሞ፣ በሰገን ህዝቦች፣ በአርሲ እና ባሌ፣ በጉጂ እና ቦረና፣ በኖጎብ፣ በአፍዴር እና በሊበን ዞኖች፣ በፋፈን፣ በሲቲ፣ በአፋር ክልል ዞን 03 እና በደቡብ ወሎ ዞኖች ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ ስርጭት የነበራቸው ሲሆን፤ የተቀሩት አካባቢዎች ላይ ከመደበኛ በታች የሆነ ዝናብ ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡


ካርታ 1  እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2   እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2018 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ3   ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን
ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



# እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21-31/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ

ባሳለፍነው የኦክቶበር የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት በመደበኛነት ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ በሚያመዝንባቸው የሰሜን፣ የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛውና የምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በጣም ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ ያመዘነባቸው እንደነበረ የተተነተኑ የአግሮ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አብዛኛው የሰሜንና የሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ከጥቂት ኪስ ቦታዎች በስተቀር ደረቃማና ከፊል ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ አመዝኖባቸው ነበር፡፡ ይህም ሁኔታ በተለይም የደረሱ ሰብሎችን ለመሰብሰብና የድህረ ሰብል ስብሰባን ለማከናወን ምቹ እንደነበረ ይታመናል፡፡ በሌላ መልኩ ግን ዘግይተው ለተዘሩ፣ እድገታቸውን ሙሉ በሙሉ ላላጠናቀቁና ተጨማሪ እርጥበት ለሚፈልጉ የመኸር ሰብሎች አሉታዊ ጎን ነበረው፡፡ በአንፃሩ እርጥበታማው ሁኔታ በምዕራብ፣ በደቡብና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ ጥንካሬ የነበረው ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ የእድገት ደረጃቸውን ላልጨረሱ የመኸር ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት ለደቡብና ለደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ለሚያከናውኑት የእርሻ ስራ እንዲሁም በደቡብና በደቡብ ምስራቅ ቆላማ አካባቢዎች ለሚገኙ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለመጠጥ ውሀና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት በጎ ጎን ነበረው (ካርታ 4)።


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ



# እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21-31/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደርው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 21-31 ኦክቶበር 2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ በተመለከተ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብና በጥቂት የመካከለኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ተስተውሏል፡፡ ይህንን ሁኔታ ተከትሎ የመካከለኛው ባሮአኮቦ፣ አብዛኛው አባይ፣ የመካከለኛው ስምጥሸለቆ፣ የገናሌዳዋ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ዋቢሸበሌ፣ መካከለኛው ስምጥሸለቆ፣ ጥቂት የላይኛውና የመካከለኛው አዋሽ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ የሆነ የእርጥበት መጠን አግኝተዋል፡፡ በሌላ በኩል የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ከከፊል ደረቅ እስከ መጠነኛ እርጥበት ተስተውሎባቸዋል(ካርታ5)።

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2018 ድረስ በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን



# እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1-10/2018 የሚኖረው

# የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በኖቨምበር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ የሚያመዝን ሲሆን፤ በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ፣ በደቡብ ምሥራቅና በመካከለኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ይዘወተራል።

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በደቡባዊው አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አልፎ አልፎ ሊጠናከሩ እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በመሆኑም በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በአብዛኛው የበጋው ደረቃማ የአየር ሁኔታ እንደሚያመዝን የሚጠበቅ ሲሆን፤ በተጨማሪም በአንዳንድ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ሊጠናከር እንደሚችል ይጠበቃል። ከዚህም ሌላ ከኦሮሚያ ዞኖች ምዕራብና ምሥራቅ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ አርሲና ባሌ፣ እንዲሁም የጉጂ እና የቦረና ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የአሶሳና የከማሺ ዞኖች፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የወላይታ፣ የዳውሮ፣ የጋሞጎፋ፣ የከፋና የቤንች ማጂ፣ የደቡብ ኦሞ እና የሰገን ሕዝቦች፤ በሶማሌ ክልል የሚገኙት አፍዴር፣ የጎዴ እና የሊበን ዞኖች በተለያዩ ሥፍራዎቻቸው ላይ በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ ያገኛሉ። የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች ደረቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ይቆያሉ።

# እ. ኤ. አ ከኖቬምበር 1-10/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

# አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ በኖቬምበር የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገራችን አካባቢዎች ላይ ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ የሚስተዋል ሲሆን፣ በሌላ መልኩ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብና በደቡብ ምስራቅ እንዲሁም በመካከለኛው አካባቢዎች ላይ መጠነኛ የሆነ እርጥበት የሚያገኙበት ጊዜ ነው፡፡ በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ መሠረት በሚቀጥሉት የኖቬምበር የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት በአብዛኛው የበጋው ደረቃማው የእርጥበት ሁኔታ እንደሚያመዝን የሚጠበቅ ሲሆን፣ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ደጋማ አካባቢዎች የሌሊቱና

የማለዳው ቅዝቃዜ ሊጠናከር እንደሚችል በትንበያው ተመልክቷል፡፡ ደረቃማው የእርጥበት ሁኔታ በተለይም የመኸር ሰብል ለሚሰበስቡና የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለሚያከናውኑ አካባቢዎች አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሮች ይህንኑ ምቹ ሁኔታ ከግምት በማስገባት የደረሱ ሰብሎችን በአግባቡና በጊዜው እንዲሰበስቡ ይመከራሉ፡፡ በተጨማሪም ከደረቃማው ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ጠንካራ ሊሆንና የውርጭ ክስተትንም በአንዳንድ አካባቢዎች ሊያስከትል ስለሚችል ይህም ሁኔታ በተለይም በአበባና ፍሬ በመሙላት ላይ ያሉ ሰብሎችን ሊጎዳ ስለሚችል አርሶ አደሮች አስፈላጊውን ጥንቃቄ ለማድረግ እንዲችሉ የግብርና ባለሙያዎች ቅርብ ክትትልና አስፈላጊውን እገዛ እንዲያደርጉ ከወዲሁ ይመከራል፡፡ በአንፃሩ ከሚጠናከሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በተለይም የደቡባዊ አጋማሽ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ እርጥበት እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ ይህም የሚጠበቀው መጠነኛ እርጥበት በተለያየ እድገት ላይ ለሚገኙ የበጋ ወቅት ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት በጎ ሚና ይኖረዋል፡፡